21ኛ አመት ቁጥር 16

21th Year No 16

ባህር ዳር መጋቢት 16 ቀን 2008 ዓ.ም

Bahir Dar 25th March 2016

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ-ሕግ

ZIKRE-HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 84.90 Unit Price in Birr	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE	የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box

ማውጫ	CONTENTS
ደንብ ቁጥር 139/2008 ዓ/ም	**Regulation No. 139/2016**
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባህር ዳር አካል ጉዳተኞች ተሃድሶ አገልግሎት ማዕከል ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	The Amhara National Regional State Bahir Dar Center for Physically Disabled Persons' Rehabilitation Service Establishment, Council of Regional Government Regulation

ደንብ ቁጥር 139/2008 ዓ/ም	**Regulation No. 139/2016**
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባህር ዳር አካል ጉዳተኞች ተሃድሶ አገልግሎት ማዕከልን ለማቋቋም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE BAHIR DAR CENTER FOR PHYSICALLY DISABLED PERSONS' REHABILITATION SERVICE IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ ለአካል ጉዳተኞች እስካሁን ድረስ የሚሠጠው የተሃድሶ አገልግሎት ቀደም ሲል በተለያዩ አጋጣሚዎች በተቋቋሙና በውጭ ለጋሾች በጐ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ግብአት በሚያገኙ የተሃድሶ ማዕከላት አማካኝነት ከመሆኑ የተነሣ ጉልህ የተደራሽነትና የጥራት ችግር ያለበት ሆኖ በመገኘቱ፤

Whereas, due the fact that the rehabilitation service which has hitherto been provided for those persons with physical disabilities throughout the national regional state happens to be carried out by the rehabilitation center which had previously been set up on several occasions and thereby generated inputs from external donors upon one's good will, it has been found out that such a service has a splendid accessibility and quality problem thereof;

ከዚህ የተነሣ ችግሩን በተጠቃሚው ህብረተሰብ ቀጥተኛ ተሳትፎና በራስ አቅም ለዘለቄታው በመቅረፍ ጥራት ያለው የተሃድሶ አገልግሎት ማግኘት ለሚገባቸው ዜጐች መስጠት የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

Whereas, due to this initiative, it has been found necessary to facilitate a condition in which the quality rehabilitation service might be provided for those citizens deserving same by having resolved the problem sustainably through direct participation of the user community and self reliance;

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ /58/ ንዑስ አንቀፅ /7/ እና በክልሉ መንግስት አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 230/2008 ዓ.ም አንቀጽ /24/ ንዑስ አንቀጽ /10/ ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Art. /58/ Sub-Art. /7/ of the Revised National Regional Constitution and Art. /24/, Sub-Art. /10/ of the Regional State Executive Organs' Establishment Proclamation No. 230/2015, hereby issues this Regulation.

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የባህር ዳር የአካል ጉዳተኞች ተሃድሶ አገልግሎት ማዕከል ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 139/2008 ዓ. ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. **"የአካል ተሃድሶ አገልግሎት"** ማለት ለአካል ጉዳተኞች አስፈላጊ የሆኑ ሰው ሰራሽ መሣሪያዎችን በማሟላት የጉዳተኞችን አካላዊ ምቾት በመጠበቅ እና ስነ-ልቡናቸውን በመንከባከብ ሁለንተናዊ ተሣትፏቸውን ከፍ ለማድረግ ታስቦ በሰለጠኑ ባለሙያዎች የሚከናወን ተግባር ነው፤

2. **"የአካል ተሃድሶ ማዕከል"** ማለት የሰዎችን የተጐዳ አካል መልሶ የማስተካከል ተግባር የሚከናወንበት፣ የሰው ሰራሽ የአካል ድጋፍ ወይም ይህንን የመሳሰሉ ቁሣቁሶች የሚመረቱበትና አካልን የማሸት ወይም

PART ONE

GENERAL PROVISIONS

1. Short title

This Regulation may be cited as "The Bahir Dar Center for Persons with Physical Disabilities Rehabilitation Service Establishment, Council of Regional Government Regulation No. 139/2016."

2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this regulation:

1. "**Physical Rehabilitation Service**" shall mean a task to be carried out by trained professionals with the intention of increasing the full participation of the physically impaired persons by having them equipped with the necessary artificial tools, maintained the physical comfort of the impaired persons and duly cared for their psychological well-being;

2. **"Physical Rehabilitation Center**" shall mean any facility wherein the activity of realigning or fixing the injured organ of a person is performed, artificial physical support or any other similar material is manufactured and physical massage or

የፊዚዮቴራፒ ህክምና እና ስልጠና እንዲሁም የሥነ-ልቡና ምክር አገልግሎት የሚሰጥበት ማናቸውም ተቋም ነው፤

3. **"ኦርቶፔዲክስ"** ማለት በዚህ ደንብ መሠረት በተቋቋመው ማዕከል ውስጥ ሰው ሰራሽ አካሎችን ወይም የአካል ድጋፎችን የማምረት፣ የመገጣጠም ወይም የመጠገን ተግባር ሲሆን በተገጠሙላቸው ወይም ተለክተው በተሰሩላቸው የአካል ድጋፎች በአግባቡ ይጠቀሙባቸው ዘንድ አካል ጉዳተኞችን ተቀብሎ የማሰልጠኑን ወይም የማለማመዱን ማናቸውንም አገልግሎት ይጨምራል፤

4. **"ቢሮ"** ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሲሆን የተዋረድ አካላቱን ይጨምራል፤

5. **"ቢሮ ኃላፊ"** ማለት የዚሁ ቢሮ ኃላፊ ነው፡፡

physiotherapeutic treatment and training as well as counseling services are provided therewith;

3. "**Orthopedics**" shall mean a task of manufacturing, installing or repairing of artificial implants or physical support items within the Center established pursuant to this regulation and includes any service of admitting persons with physical disabilities and thereby training or causing them to exercise so that they would properly use those physical support items structured with them or produced in accordance with their size;
4. "**Bureau**" shall mean the Amhara National Regional State Labour and Social Affairs Bureau and includes its subordinate structures;
5. "**Bureau Head**" shall mean the Head of this Bureau.

3. ስለ መቋቋምና ተጠሪነት

3. Establishment and Accountability

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህር ዳር የአካል ጉዳተኞች ተሀድሶ አገልግሎት ማዕከል ከዚህ በኋላ **"ማዕከሉ"** እየተባለ የሚጠራ ህጋዊ ሰውነት ያለውና ራሱን የቻለ የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁመዋል፤

1. The Amhara National Regional State Bahir Dar Center for Persons with Physical disabilities Rehabilitation Service /hereinafter referred to as **"the Center"**/ is hereby established under this regulation as an autonomous regional government office having its own legal personality;

2. የማዕከሉ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል።

4. ዓላማ

የማዕከሉ አይነተኛ ዓላማ በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ ለሚገኙ አካል ጉዳተኛ ዜጐች ከጉዳተኝነታቸው ጋር የተያያዘ ሁለንተናዊ የአካል ተሀድሶ አገልግሎቶችን ያለአንዳች ልዩነት መስጠት ይሆናል።

5. ዋና መስሪያ ቤት

የማዕከሉ ዋና መስሪያ ቤት በባህር ዳር ከተማ ሲሆን ለስራው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በክልሉ ውስጥ በሌሎች ስፍራዎች ማስተባበሪያ ጣቢያዎችን ሊያቋቁም ይችላል።

ክፍል ሁለት

ስለ ማዕከሉ ተግባር፣ አደረጃጀትና አመራር

6. የማዕከሉ ተግባርና ኃላፊነት

ማዕከሉ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ሀላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. ዝርዝሩ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ የሚደነገግ ሆኖ በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ አካል ጉዳተኞች ሁሉን አቀፍ፣

2. The Center shall be accountable to the Bureau.

4. Objective

The typical objective of the Center shall be to provide an all-out physical rehabilitation service for the citizens with physical disabilities found throughout the National Region in connection with their disability and without any distinction.

5. Head Office

The Head Office of the Center shall be in the City of Bahir Dar provided that it may establish coordinating stations in other places within the Regional state, as deemed necessary for the duty thereof.

PART TWO

DUTIES, ORGANIZATION AND MANAGEMENT OF THE CENTER

6. Duties and Responsibilities of the Center

The Center shall, pursuant to this regulation, have the following specific duties and responsibilities:

1. with the details to be provided for by a directive issued for the implementation of this Regulation, render all-embracing, efficient and standardized physical

ቀልጣፋና ደረጃውን የጠበቀ የአካል ተሀድሶ በተለይም የኦርቶፔዲክስና የፊዚዩቴራፒ አገልግሎቶችን እንደተገቢነቱ በነፃ ወይም በተመጣጣኝ ክፍያ ይሰጣል፤

2. በራሱ አነሣሽነት ወይም ከተገልጋዩች በሚቀርቡለት ጥያቄዎች መሠረት ብረት፣ ፕላስቲክና ሌሎች ጥሬ እቃዎችን በመጠቀም ሰው ሰራሽ አካሎችን ወይም ክራንቾችን፣ ተሽከረካሪ ወንበርና ነጭ በትር የመሳሰሉትን የተለያዩ የአካል ድጋፎች በጥራት ያመርታል፣ እንደአስፈላጊነቱ ይጠግናል፣ በነዚሁ መሣሪያዎች ወይም ቁሣቁሶች ባግባቡ ይገለገሉባቸው ዘንድ ተገጅዎችን ተቀብሎ ያሰለጥናል፣ ያለማምዳል፤

3. የሚሰጠውን የስልጠና መርሃግብር በአግባቡ ተከታትለው ላጠናቀቁ እጩ ምሩቃን የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

4. በዚህ ደንብ መሠረት ለሚሰጣቸው የአካል ተሃድሶ አገልግሎቶች ከውጭ በዕርዳታ የሚመጡ የኦርቶፔዲክስ ግብአቶችን በክልሉ ውስጥ ለማምረት ተግቶ ይሠራል፣ ክልላዊ የተሃድሶ ቴክኖሎጂ ምርምር ማዕከል በመሆን የአካባቢ ቴክኖሎጅዎችን ያሳድጋል፤

rehabilitation with specific reference to orthopedics and physiotherapeutic services for the persons with physical disabilities found in the Regional State with no charge or a reasonable payment, as appropriate;

2. upon its own initiation or the request to be otherwise submitted to it by those in need of the service, manufacture artificial limbs or crunches with the required quality, wheelchairs, white canes and various physical support items of the like nature by having utilized metal, plastic and other raw material, repair same, as deemed necessary, as well as admit the disability, train and cause them exercise so that they would be able to properly use such equipment or material thereof;
3. issue certificates for candidate graduates who may have properly pursued and completed the training program provided thereof;
4. diligently strive towards the production of orthopedic inputs imported from abroad by way of assistance the form of aid to be rendered for the physical rehabilitation services pursuant to this regulation in the region and thereby develop local technologies having assumed the status of the regional rehabilitation technological research center;

5. አካል ጉዳተኝነትን በመከላከልና የተሃድሶ አገልግሎትን በማስፋፋት ረገድ ለክልሉ ህብረተሰብ የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት ይሰጣል፤

6. አካል ጉዳተኞች እና ቤተሰቦቻቸው በሽታዎችን በመከላከልና በጤና እንክብካቤ ላይ ያተኮረ ወቅታዊ መረጃዎችን እንዲያገኙ ያደርጋል፤

7. በአካል ጉዳተኝነት ዙሪያ ከሚሰሩ አጋር አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣ በዚህም አማካኝነት አካል ጉዳተኞች የተሟላ የተሃድሶ አገልግሎት ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ያደርጋል፤

8. በህግ በተፈቀደው አኳኋን የገቢ ማስገኛ ስልቶችን በመቀየስ ሃብቶችን ያፈላልጋል፣ ያሰባስባል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤

9. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውሎችን ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል።

7. ስለ ማዕከሉ ድርጅታዊ አቋም

1. ማዕከሉ በዞን መምሪያ ደረጃ የሚዋቀር ሆኖ የራሱ ስራ አስኪያጅ፣ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ይኖሩታል፤

5. provide awareness raising education for the community throughout the region in relation to the prevention of disability and the promotion of rehabilitation services;

6. see to it that persons with disabilities and their respective families have access for timely information in respect of the disease prevention and health care;

7. work in collaboration with stakeholders operating on disability issues and hence cause persons with disabilities become the beneficiaries from the utilization of a foliaged rehabilitation service;

8. seek for, mobilize and expend resources by having devised income-generating strategies in a manner as permitted by law;

9. own property, enter into contracts as well as sue or be sued in its own name.

7. Organizational Structure of the Center

1. The Center shall, having been structured at the level of a zonal department, have its own manager, professionals required for the duty and support staff;

2. ማዕከሉ ስራ አስኪያጁንና የየስራ ክፍሎቹን ኃላፊዎች ያካተተ የስራ አመራር ኮሚቴ ይኖረዋል።

2. The center shall have a management committee comprising the manager and heads of each and every division.

8. ስለ ማዕከሉ ስራ አስኪያጅ አሿሿምና ተጠሪነት

1. የማዕከሉ ስራ አስኪያጅ በዞን መምሪያ ሃላፊ ደረጃ በቢሮ ኃላፊው ይሾማል፤

2. የሥራ አስኪያጁ ተጠሪነት ለቢሮ ኃላፊው ይሆናል።

8. Appointment and Accountability of the Manager of the Center

1. The manager of the center shall be appointed by the Bureau Head with the rank of a zonal department head;
2. The manager shall be accountable to the Bureau Head.

9. የስራ አስኪያጁ ስልጣንና ተግባር

1. የማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ በዚህ ደንብ አንቀጽ /6/ ስር ለማዕከሉ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች በስራ ላይ ያውላል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ስራ አስኪያጁ ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ. በዚህ ደንብ ድንጋጌዎችና ከቢሮው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የማዕከሉን የዕለት ተለት ስራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

9. Powers and Duties of the Manager

1. The manager of the center shall put into effect the duties and responsibilities given to the Center under Art. /6/ of this Regulation hereof;

2. Without prejudice to the general provision stipulated under Sub-Art. /1/ of this Article hereof, the Manager shall have the following specific powers and duties:

A. direct, coordinate and supervise over the day to day activities of the center in accordance with the provisions of this Regulation and the directive to be given to him by the Bureau;

ለ. የማዕከሉን ሠራተኞች በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

B. recruit, administer and dismiss employees of the Center in accordance with the Regional civil service laws, regulations and directives;

ሐ. የማዕከሉን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፣ በስራ አመራር ኮሚቴው ደረጃ ከተመከረበት በኋላ ለቢሮው ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

C. prepare the draft annual work plan and budget of the Center, summit same to the Bureau after the managerial committee has deliberated upon it and thereby implement same upon prior authorization thereof;

መ. ለማዕከሉ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ እንዲሆን ያደርጋል፤

D. cause the disbursement of money in accordance with the budget approved for the Center and its work program thereof;

ሠ. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ማዕከሉን ይወክላል፤

E. represent the Center in its dealings with third parties;

ረ. የማዕከሉን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ወቅታዊ ሪፖርቶችን እያዘጋጀ ለቢሮው ያቀርባል፤

F. prepare periodic reports regarding the activities of the center and submit same to the Bureau;

ሰ. በቢሮው የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

G. perform such other related duties as may be rendered to him by the Bureau.

10. ስለ ማዕከሉ ሙያተኞች ደረጃና ጥቅማጥቅም

በማዕከሉ ውስጥ በኦርቶፔዲክስ፣ በፊዚዮቴራፒ እና በስነ-ልቡና ምክር አገልግሎት የሙያ መደቦች ላይ የሚያገለግሉ ባለሙያዎች በክልሉ ውስጥ ለአካል ተሃድሶ ማዕከላት በተፈቀደው አግባብ የሙያ ዕድገት መሠላል ተጠቃሚዎች ይሆናሉ።

11. የቢሮው ልዩ ስልጣን

ቢሮው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች አተገባበር አስመልክቶ የሚከተሉት ልዩ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የማዕከሉን አጠቃላይ ስራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤
2. በስራኪያጁ ተዘጋጅተው ሲቀርቡለት የማዕከሉን ስትራቴጅያዊና አመታዊ የስራ ዕቅዶችና የማስፈፀሚያ መርሀ-ግብሮች መርምሮ ያፀድቃል፤
3. ይህንን ደንብ መሠረት በማድረግ የማዕከሉን ተልዕኮ ለማሳካት አስፈላጊ ሆነው የተገኙትን ሃብቶች በተለያዩ ዘዴዎች ያሰባስባል፤
4. ማዕከሉ በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰጣቸው ማናቸውም አገልግሎቶች ፍላጐቱ ላላቸው ለሁሉም ዜጐች ያለአንዳች አድልኦ ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

10. Position and Benefits of the Professionals of the Center

Professionals serving in occupational positions of orthopedic, physiotherapy and counseling services in the center shall be benefit from the professional career structure in such a manner as has been permitted for the Regional Physical Rehabilitation Center.

11. Special Powers of the Bureau

The Bureau shall have the following special powers and duties with regard to the implementation of the provisions of this Regulation:

1. manage and coordinate the general activities of the Center;
2. examine and approve the strategic and annual work plans along with the implementation programs following their preparation on the part of the Manager;
3. mobilize resources, using various methods, found to be necessary in view of attaining the mission of the Center pursuant to this regulation;
4. ensure that any service to be provided by the Center pursuant to this regulation is accessible to all citizens who wish secure same without any discrimination;

5. በማዕከሉ ስራ አስኪያጅ አማካኝነት በየጊዜው የሚቀርቡለትን የስራ ሪፖርቶች ይመረምራል፣ ውሣኔዎችን ያሳልፋል፤

6. የማዕከሉ ሀብትና ንብረት በሚገባ መያዙንና ለተፈላጊው ዓላማ በጥቅም ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ጥፋት ተፈፅሞ ሲገኝም የእርምት ዕርምጃዎችን ይወስዳል።

ክፍል ሶስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

12. የገቢ ምንጭ

የማዕከሉ ገቢ ከሚከተሉት የሚመነጭ ይሆናል፡-

1. በክልሉ መንግስት የሚመደብ በጀት፤

2. ማዕከሉ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚሰበሰብ ክፍያ፤

3. ከተለያዩ አካላት በዓይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ መልክ የሚገኝ ድጋፍ፤

4. ከሌሎች ምንጮች።

13. የሂሣብ መዛግብትና ኦዲት

1. ማዕከሉ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶችን ይይዛል፤

5. examine activity reports periodically submitted it by the Manager of the Center and make decisions thereon;

6. monitor that the resource and property of the center is properly handled and employed for the desired objective and take corrective measures on account of wrong doing;

PART THREE

MISCELLANEOUS PROVISIONS

12. Source of Income

The income of the Center shall be generated from the following:

1. Budget to be allocated by the Regional government;

2. Charges to be collected out the services provided by the Center;

3. Support to be obtained in kind and in cash from various bodies;

4. Other sources.

13. Books of Account and Auditing

1. The Center shall maintain complete and accurate books of account and documents.

2. የማዕከሉ ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ወይም ቢሮው በሚሰይመው አካል በየጊዜው ይመረመራሉ።

14. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጐች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

15. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ቢሮው ይህንን ደንብ በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

16. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

መጋቢት 16 ቀን 2008 ዓ.ም

ገዱ አንዳርጋቸው

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ርዕሰ መስተዳድር

2. The financial as well as property related documents of the Center shall be annually audited by the Office of the Auditor General of the Regional State or a body to be designated by the Bureau.

14. Inapplicable Laws

No other regulation, directive or customary practice inconsistent with this regulation shall be applicable with respect to the matters covered therein.

15. Power to Issue Directives

The Bureau may issue directives necessary for the full implementation of this Regulation.

16. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar

This 25th day of March, 2016

Gedu Andargachew

Head of Government of the

Amhara National Regional State